ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምጽ
Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity
Efdpu@aol.com www.Finote.org

Tel 202291 4217 mailling address: P.O.Box 73337, Washington Dc 20011

በፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ራዲዮ
በየካቲት 30, 2009 ዓም የተላለፈ ሐተታ

# የወንዙን ዉሃ ምን ያስጮኸዋል?

ከውስጥ ስሜትና ከውጭ ተጽዕኖ በመጣ ምክንያት፤ሰው ሊጮኽ ይችላል ፡፡ አቤቱታ ለማሳማት፤ ርዳታ ለመጠይቅ፤ ከስቃዩ ለመገላገል፤ ሀዘን ደስታውን ለማካፈል፤ ሲጨንቀው ሲጠብበው እፎይታ ለማግኘት ሲል ሰው ይጮኻል ። ጮኸት የደስታና የሃዘን ምልክት መግለጫ ሆኖ ቆይቷል። ዕሪታ ለአደጋና ለሃዘን ፤ እልልታ ለምስራችና ለሀሴት - ምልክቶች ሆነው ሲያገለግሉ ኖረዋል ። ልጅ ሲወለድ ዕልልታ፤ ሰው ሲሞት ኡኡታ ማሰማት የህብረተሰባችን ባኅል ነበር። አሁንም ነው። እልልታ በሃሴት ሲታጀብ፤ ኡኡታ ደግሞ ድንጋጤን፤ ሽበር- ጭንቀትን - ፍርሃትን ሀዝንን አስከትሎ ይመጣል ፡፡ ጩኸት፤ ለአቤቱታ መግለጫም ያገለግላል።

የቅርቡ ታሪካችን ግን ኡኡታን እንጅ ዕልልታን የመስማትም ሆነ የማሰማት ዕድል አላገጠመውም ። በማህበራዊ ኑሯችን ውስጥ ዕልልታና ኡኡታ ተፈራራቂ ሆነው የቆዩ ቢሆንም ፤ የቅርብ ታሪካችን ግን የኡኡታን መርዶ እንጅ የእልልታን ምሥራች አብስሮ አያውቅም። በዘለቄታ መልኩ መቀጠል አለበት ተብሎ የጭካኔ ፍርድ የተበየነበት ይመስል፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ ፤ በህይወቱ፤ እልልታ ሲናፍቀው ፤ ኡኡታ ሲያንገፈገፈው ኖሯል ። በረሃብ ሲጠቃ ኡኡታ ፤ ሲዘረፍ ኡኡታ ፤ ቀማኛ ሲነጥቀው ዑዑታ ፤ ገዥዎቹ ሲበድሉት ዑዑታ! ለዚህም የመስላል፤ " **ተሸካሚ ሆንኩኝ መከራና ጥጣ፤ የሚያወርድልኝ ኃይል ወዴት ሄጀ ላምጣ** ? " እያለ የሚያንጎራጉረው !

ዛሬ የኢትዮጵያ ሕዝብ ፤ያገር ያለህ ! የዳኛ ያለህ ! የህግ ያለህ! የመንግሥት ያለህ ! እያለ ይጮኻል። ሀገርም ፤ ዳኛም፤ መንግሥትም እንደሌለው ልቡ እያወቀው ፤ ጩኸቱን የሚሰማለት አገኛለሁ ብሎ ግን ዕሪታውን ቀጥሏል ። ሀገርና ሕዝብ አኩርፈዋል ። ተቀይመዋል። ተቀያይመዋል ። ተሸሽገዋል ። ተደብቀዋል ። መላ-ቅጡ ጠፍቷቸዋል። ቅስማቸው ተሰብሮ፤ አንገታቸውን ደፍተዋል ። ሰማይ -ምድሩም ተደፍቶባቸዋል ።እርስ- በእርሳቸው እንዳይወያዩ፤ እንዳይመካከሩ፤ ፊት ተዘዋውረዋል ። ተኮራርፈዋል ። የጋራ መንግሥትና ህግ፤ ዳኛና ፍትኅ-ርትዕ በመጣታቸው፤ በአውላላ ሜዳ ላይ ይማልላሉ ። ይዋልላሉ። አቃፊ-ሰብሳቢ መንግሥት አጥተው፤ በበታኝ ሥርዓት፤ ተበታትነዋል ። ከሀገራቸው ዕትብት ጋር እንዲቆራረጡ እየተደረጉ ነው። ሀገራቸውም፤ ስሟ ብቻ እንጅ፤ ጨገሬታዋ እንደለለ ተቆጥሯል ። ኢትዮጵያና ሕዝቧ ጮኸታቸውን የሚያዳምጥላቸው ታዛቢ አላገኙም ።

በዚህ ምክንያት ፤ ዕሪታቸው ሁሉ፤ የገደል ማሚቶ ሆኖ ቀርቷል ። ሰሚ ያጣ ጩኸት ! ተስፋ አስቆራጭ ዋይታ! የተቃውሞ ሠልፍ ጫጫታ፤ የዐቤቱታ ደብዳቤ ጋጋታ፤ ለውጭ መንግሥታት ዋይታ ፤ ለሰብዓዊ መብቶች ጥሰት

ተከራካሪዎች ስሞታ፤ ለግብረ-ሠናይ ድርጅቶች ልመና ሁሉ የሠላማዊ ትግል አካሎች ናቸው ቢባሉም ፤ ግን ፤ብቻቸውን ፤ ፋይዳ አላስገኙልንም ። እስካሁን ድረስ !

ብልሃትንና ዘዴን፤ ከጉልበት ጋር አቅኛጅተን ካልጮኸን ፤ ካልታገልን፤ ጮኸታችንን ማንም ከቁም-ነገር እንደማይቆጥርልን ማመን አለብን። ይኸንን ዘረኛ አጋዛዝ ማስወገድ የምንችለውም፤ ሁለቱን አሟልተን ስንገኝ ብቻ ነው ። **ብልሃትና ጉልበት!** ብልሃት ፤ ከሕዝብ ዕውቀት ይመናጫል። ኃይል ደግሞ፤ ከሀገር አንድነትና ውህደት ይገኛል ።

ሁሉም ነው ማለት ቢከድም ፤ ቁጥሩ የማይናቅ ክፍል ግን፤ በየቤቱ " ጆሮ -ዳባ ልበስ " ብሎ የተኛ በመሆኑ፤ መስማትም ሆነ ማሰማት እንደማይፈልግ ሆኖ ተቀምጧል ። ደንዝዟል ። ፈላጊ ፤ ተፈላላጊና አፋላላጊ አለተገናኙም። የመኖር ተስፋው ተሟጥጦ፤ ጭላጩን እያንጠፈጠፈ መቆየቱን መርጧል ። ችግሩ፤ ውርደቱ፤ ጥቃቱ፤ ችንፈቱ፤ በየአንዳንዱ ዜጋ ቤት ፤ እያንኳኳ መሆኑን ቢረዳውም ፤ " የባሰ አታምጣ !" ከማለት በስተቀር ፤ የተለየ መልስ ለመስጠት የተዘጋጀ አልሆኑም ። መንግሥትና ህግ በሌሉበት ሀገር ፤ሕዝብ ተወያይቶ፤ ተነጋግሮ፤ ተግባብቶ የራሱን ኅበዝ-ዐለቃና መሪ እየመረጠ- እያወጣ ፤ከጥቃት የሚላቀቅበትን ዘዴ ለመፈልግ እንኳን አልተቻለው ። ይኸንን ዘዴ ማግኘት ወሳኝ ነው!

በተቀዋሚው ጎራ ተኮልኩሏል የሚባልለት ሁሉም፤ እንኳንስ የሕዝቡን ዕሮሮ ማሰማት ይቅርና፤ የየራሱን ችግር ሊወያይ የሚቻለበትን ዘዴና ብልኀት ሊፈልግ አልተቻለውም ። በራሱ አነሳሽነት የራሱን ዓላማ፤ ዕቅድ ፤ ስልት፤ ስትራተጂና ራዕይ ነድፎ፤ በራሱ ጉልበትና ሂደት መንቀሳቀስ ተስኖት፤ ከወያኔ የሚወረወርለትን ምጽዋዕትና ዳረጎት ይጠባበቃል ። በፖለቲካ ምፅዋዕት ፤ በኢኮኖሚ ርጥባን የሚኖር ኅብረተሰብ፤ሰማይ ምድሩ ስለሚደፋበት ፤ ከሰቆቃው ለመውጣት የሚያስችለውን ራዕይ ለማየት አይችልም። በዕለት ዕለት የኑሮ ችግር ተውጧልና ! አምባገነን ሥርዓት ፤ ይኸንን ሁኔታ ይፈጥራል ። ይኸ ሁኔታ ደግሞ፤ ሕዝብን ርግጦና አሽመድምዶ ለመግዛት ያመቸዋል ። ልዩ ልዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች ፤ለጊዜው ጨቋኝ ሥርዓቱን የሚቋቋሙበት ጉልበቱንም ሆነ ብልኀቱን አላገኙትም ። መልኀቋን እንዳጣች መርከብ፤ አቅጣጫና ራዕይ ተሰውሮባቸዋል። ጉልበቱንና ብልሃቱን ያስማረከ ሕዝብ ፤የተገፈፈ ነፃነቱን ለማስመለስ ብዙ ውጣ -ውረድ ይገጥመዋል ።

ዜጎቻችን ፤ በልኀቱንም ሆነ ኀልበቱን ባለማግኘታቸው ሊፍረድባቸው አይገባም ። እንዲያውም ይታዘንላቸዋል ! የማይፈረድባቸው በሁለት ምክንያቶች ነው ። የ17 ዓመታት የደርግ አረመኔ አጋዛዝና የ26ቱ ዓመታት የዘረኞች አጋዛዝ ፤ ያስከተሉት ሽበር፤ ትወልዱን የአካል የአዕምሮ ፤ የመንፈስና የኅሊና ስብራት ሰልባ አድርጎት ቀርቷል ። ፍርሀትና መሽማቀቅ ሰፍኗል። ለአለፉት ግማሽ ምዕተ-ዓመት፤በትውልዱ ላይ ሁለንተናዊ በደል ተፈጽሞበታል ። ተዘርዝሮ የማይልቅ ፤ ወንጀል ተሰርቷል። በዜጎች መካከል ፤ በራስ የማመንም ሆነ ፤ እርስ በእርስ የመተማመን ሁኔታ ደብዛው እንዲጣፋ አድረገውታል ። እርስ በእርስ የመተማመንና ራስንም የማመን ሁኔታ ከሌለ ደግሞ፤ ሀገርን በሚመለከት አንዳችም ቁም-ነገር ይሰራል ተብሎ አይጠበቅም። ወታደራዊው አምባገነና ዘረኛ አጋዛዞች የጣሉት ጠባሳ በቀላሉ የሚጠፋ አይሆንም ። ዘረኝነትን ለማስፋፋት የቆሙትን ለማጥፋት ከተፈለገ፤ በግድ ሁለት መሠረታዊ ነገሮች ተባብረው መምጣት የኖርባቸዋል ። በዛሬይቱ ኢትዮጵያ፤ ሁለቱም የሉም ።

በአሁኑ ወቅት፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሁለት ዐበይት ጉዳዮችን አጥቷል ። እነ እርሱን ካላገኘ ደግሞ ከችግሩ በምንም ዓይነት መንገድ ሊወጣ ከቶ አይቻለውም ። እነኝህን ዐብይ ጉዳዮች ማግኘት መሠረታዊና አጣዳፊ መሆናቸውን ካልተገነዘበ

ደግሞ፤ የታሪክ እስረኛና የአምባገነኖች መጫዎቻ ከመሆኑ አይድንም። እነኝህ መሠረታዊ ጉዳዮች፤ **ጎልበትና ብልሃት ናቸው።** ጉልበትና ብልኅት ዛሬ በኢትዮጵያ ምድር የሉም። አልተገኙም ። ደብዛቸው ከጠፉ ዓመታት ተቆጥረዋል ። ብልሃት አልባ የሆነ ሕዝብ አቅመ ቢስ -ደካማ መሆኑ ደግሞ ሳይታለም የተፈታ ነው። የአዕምሮ ጤንነት፤ የኅሊና ነፃነት፤ የሰብዕና ማንነት፤ ባልተሟላበት ኅብረተስብ ውስጥ፤ ብለኅትና ጉልበት የሉም ። ቢፈለጉም አይገኙም ።

ሁለቱን አሟልቶ ያልተገኘ ሕዝብ ደግሞ፤ ሊኖር የሚችለው ሕይወት፤ ለመኖር ብቻ ሲል የሚኖር ስለሚሆን፤ ነጻናቱንና ሰብዕብናውን አሳልፎ እንደሰጠ ይቆጥራል ። የኢትዮጵያ ሕዝብ ፤ አሁን ከወደቀበት አዘቅት ለመውጣት ከፈለገ፤ ያጣውን ጉልበት፤ ኃይልና ብልኅት በግድ መልሶ ማግኘት አለበት። ዛሬ እፍኝ የማይሞሉ ዘረኞች የሚጫወቱበት፤ ብልሀቱና ጉልበቱ ስለጠፉበት ነው ቢባል ማጋነን አይሆንም ። ከጠቅላላ የሀገሪቱ ሕዝብ ቁጥር፤ ከመቶ ስድስት / 6% ብቻ እንወክላለን የሚሉ ዘረኞች፤ ከመቶ ዘጠና አራት / 94% የሚሆነውን ሕዝብ፤ እንደ ሰም አቅልጠው፤ እንደ ገል ቀጥቅጠው የሚጋዙት ምን ብልሃትና ጉልበት አግኝተው ነው ? ብሎ መጠየቅ ያስፈልጋል ። መልሱ ደግሞ ከባድ አይደለም ። ሌላው ያጣውን፤ በእነርሱ እጅ ስለገባ ነው ።

የጥንት አባቶች፤ ልጆቻቸውን ሲመርቁ " **የጉንዳንን ጉልበት ፤ የሴትን ብልሃት** " ይስጥህ ይሉ ነበር ይባላል ። ይኽ ምርቃን፤ ዛሬ ለኢትዮጵያ ሕዝብ፤ ከማነኛቸውም በጎ ምኞትና ተስፋ በበለጠ የሚያስፈልገው ይመስለናል ። ያዕምሮ ብስለትና የአካል ጥንካሬን አስተባብሮ ያሊያዘ ሕህበረተሰብ፤ ከአቅም -ግንባታ ጋር ተለያይቶ ይኖራል ። ለመጣ- ለሄደው ሁሉ መሳቂያ-መሳለቂያ ይሆናል ። ደርግና ወያኔ በመፈራረቅ የኢትዮጵያን ሕዝብ ሊበድሉት፤ ሊያሰቃዩትና ሀገሪቱንም አሁን ከደረሰችበት አሳዛኝ ደረጃ እንድትደርስ ያደርጓት ፤ ዜጎቿ አቅምንና ብልሃትን አስተባብረው ባላማያዛቸው ነበር። አሁንም ጉልብትና ብልሃት ያንሳቸዋል ። ያንን ለሟሟላት ብዙ ምዕራፍ የቀራቸዋል ። **የጎንዳንን ጎልበት ፤ የሴትን ብልሃት** ፤ አለማግኘት የቱን ያህል እንደሚጎዳ ፤ የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ዜጎች እንደ ህያው ምስክሮች ይቆጠራሉ።

" **እንደ ጦጣ ብልጥ፤ እንደ ዕርግብ የዋህ ሁን** " የሚባል የቆየ አባባል አንዳለ መኖሩን ብንገነዘብም ፤ዛሬ ሀገራችን ከገጠማት ችግር ልትወጣ የምትችለው ግን ፤ " የጉንዳንን ጉልበትና የሴትን ብልሃት "አጣምራ ስትይዝ ነው ። ወቅቱ የሚጠይቀውም ይህንኑ ነው። በአባቶቻችን/ እናቶቻችን ጀግንነትና ሙያ ብቻ እየተኩራራን መኖር የምንችልበት ዘመን አልፏል። ያለፉትን መውቅስ አስፈላጊ ከሆነ ፤ እነርሱን ከመውቀስ በፊት ፤ እነርሱ ከሰሩት የበለጠ ሥራ ሰርቶ መገኘትን ይጠይቃል ። የሞራል ልዕልና ሊያስገኝ የሚችለው፤ በዘመናቸው ሊሰሩት የቻሉትን ሰርተው ያለፉትን ሳይሆን፤ የወቅቱ ዘመን ትውልድ፤ ከእነርሱ የተሻለ ሥራ ሰርቶ ሲገኝ/ በመገኘት ነው። ይኽንን ብቁነት ለማግኘት፤ የጉንዳንን ጎልበትና የሴትን ብልሃት አጣምሮ መያዝን ይጠይቃል ። ዕቅጩን መስማት አለብን ከተባለ፡ ዛሬ፤ ጉልበቱም ሆነ ብልኀቱ ጎድሎናል ። ያንን መሟላት ይጠበቅብናል ። ከጥቃትና ወርደት ለመዳን !

በሥነፍጥረት ሚዛን ስትለካ፤ ጉንዳን ፤ እጅግ ሲበዛ ትንሽ ፍጡር ነች። በዐይን የምትገባም አይደለችም ። ትንሽ ሚጢጢ ነገር ናት ! አቅሟና ጉልበቷ ግን፤ ከመጠኗ ጋር ሲመዝን፤ 10/ አሥር እጅ ይበልጣል ። የአንድ ጎዳን ሬሳ ብቻዋን ተሸክማ ብዙ ርቀት መሄድ ትችላለች ። የሰው ልጅ፤ የሌላ ሰው ሬሳ ፤ እንኳንስ ብቻውን ተሸክሞ ሩቅ መንገድ ሊሄድ ቀርቶ ከወደቀበት ለማገላበጥ እንኳን ቢሆን በጣም ይከብደዋል ። ማንቀስቀስ አይሆንለትም ። ጉዳን የሌሎች ወገኖቿን ጥቅም

ለማስጠብቅ የምታሳየው መሥዋዕትነት ያስደምማል ። ያስገርማል ። የጉንዳን ክምችት፤ ወንዝ ሲሻገር፤ እያንዳንዱ ጉንዳን እንደ ድልድይ ሆኖ በመዝርጋት ፤ ሌላው ሁሉ በእርሱ ላይ እየተረማመደ እንዲሻገር ያደርጋል።ሁሉም መሸጋገሩን ሲያረጋግጥ በመጨረሻ ፤ የውሃው ተሻጋሪ እርሱ ይሆናል ።የሚያስገርም ኃይል ያላት ጉንዳን፤ የምታሳየው ብርታትና መሥዋዕት አስገራሚ ትምህርትን ይሰጣል ።

የሴት ብልህነት ተነግሮ፤ ተወርቶ ፤ ተጽፎ ፤ የተመሰከረለት በመሆኑ ፤ በዚህ ላይ ብዙ ማለት አይቻልም ። " ሴቶች የኅብረተሰቡ ግማሽ አካል ናቸው ! " " ያለ ሴቶች ትሳትፎ ትግሉ ግቡን አይመታም ! " " ሴቶች የቤተሰባቸው ዋልታና ግድግዳ፤ ትክሊልና አክሊል ናቸው ! " እና የመሳሰሉት ብሂሎች ፤ ከአባባል አልፈው ተርፈው፤ ዕውነተኛውን ጉዳይ ገላጮች ናቸው ። ታዲያ፤ ቀደምት አባቶች/ እናቶች፤ ልጆቻቸውን ሲመርቁ ፤ " የጉንዳንን ጉልበት የሴትን ብልሃት ይስጥህ ! " ማለታቸው፤ ከእውቀትና ተመክሮ ያካበትቱ ምርቃን ነበር ። ኅብረተሰባችን ፤ ከዘረኞች አጋዛዝ ቀንበር ለመገላገል ፍቱን መዳኅኒቱ፤ ብልሃትን ከጉልበት ፤ ጥንካሬን ከጥበብ ጋር ሸርቦ መታገል አለበት ። ይኸንን ካደረገ፤ የወያኔን ዕድሜ ማሳጠሩ ዕሙን ነው። ያ ሳይሆን እየቀረ ፤ " ወያኔ፤ መውደቂያዋ ተቃርቧል ! እያሉ ሰማይ -ሰማይ ማንጋጠጥ፤ " ደርግ አንድ ሣምንት ቀርቶታል "ሲባል ከነበረው የቀቢፀ- ተስፋ ምኞት አያልፍም ።

ወያኔ፤ ከእርሱ በፊት ከነበረው የወታደር አምባገንን በበርካታ ሁኔታዎች ይለያል ። በአፈጣጠርና ይዘት፤ በዓላማና ግብ፤ በአደረጃጀትና የተግባር አፈፃፀም ፤ የመንግሥት ቅርፅና አውቃቀር፤ ስለ ኢትዮጵያና ዜጎቿ፤ ስለ ታሪኳና ባህሏ፤ በአብሮነት መቀጠል- አለመቀተሏ ፤ ስለአለው ዕመነት ሁሉ ሲገመገም፤ የሀገራችን ስትራተጅያዊ ጠላት እንደሆነ ተርጋግጧል ። እርሱ ራሱም ቢሆን ይኸንን ሊክድ አይችልም። የተነሳበትን ዓላማ እግቡ ለማድረስ እንዲያስችለውም ፤ በገንዘብ/ በኢኮኖሚ፤ ንግድና ባንክ፤ ጉምሩክና አስመጭ ላኪ ተግባራት፤ በጦር ኃይል ፤ በስለላ፤ በመገናኛ ብዙሃን፤ በውጭ ጉዳይ/ በዐለም ዐቀፍ ግንኙነት፤ ሁሉ አጠቃልሎ በቁጥጥሩ ስር አድርጓል ።ሀገሪቱን በታሪኳ ባላጋጠማት ሁኔታ፤ በፍፁማዊ ኃይል / ቶታሊታርያን አጋዛዝ ረግጦ ይዟታል ። ለማነኛው ዓላማው መምቻ ፤ የገንዘብ ኃይል ወሳኝ መሆኑን በመረዳት፤ የሀገሪቱን ዕምቅና ተንቃሳቃሽ ሀብት በመዳፉ አስገብቶ፤ እንዳሻው ይዘርፋል ። የኅወኃት አባላትና ደጋፊዎች ፤ ከሚሊዮን እስከ ቢሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ ያዘዋውራሉ። ይጠቀማሉ፡፤ ልጆቻቸውን ወጭ ሀገር ድረስ እየልኩ ያስተምራሉ ። የሀገሪቱን ሀብት በገፍ ወደ ውጭ ያሸሻሉ።

**ኤፈርት** የተሰኘው የወያኔ የገንዘብ መዝረፊያ ድርጅት፤ የሀገሪቱን ሁለንታናዊ የንግድ ፤ የእንሹራንስ ፤ የባንክና የገበያ አውታሮቹን ሁሉ ተቆጣጥሯል ። በዚህ የገንዘብ ማፍያ ድርጅት ስር፤ አልመዳ ጨርቃጨር፤ ሞሶብ ሰሜንቶ ፋብሪካ፤ መስፍን ኢንጂነሪንግ፤ ኢዛና ወርቅ ማዕደንና ዕምነ በረድ፤ ሱር ኮንስትራክሽን ፤ ጉና ኮርፖሬሽንና ሂይወት ዕርሻ ሜካናይዜሽን በቢሊዮን የሚቆጠር የሀገሪቱን ገንዘብ ይቆጣጠራል ሁሉም ኩባንያዎች፤ ፋብሪካዎችና የገንዘብ ተቋማት የተመሠረቱት ትግራይ ውስጥ ነው። ጥሬ ሀብቱ፤ የእርሻው ስብል ወጤት ግን ከሌሎች የሀገሪቱ ክፍሎች ፤ ወደ ትግራይ እየተጓጓዘ በዚያ የተተከሉት ፋብሪካወች ይመግባል ። ከጎንደር፤ ከወሎና ከአፋር የተነጠቁት ሰፋፊ፤ ለምና በማእድናት የበልፀጉ መሬቶች፤ ወደ ትግራይ መጠቃለላቸው፤ የወያኔን የንግድና የገንዘብ አፄዐዊ (ኢምፓየር ) ለመስፋፋትና ለማረጋገጥ፤ ታስቦ የታለመ ዓላማ መምቻ ነው ። እነኝህ የወያኔ የገንዝበ የንግድና የፋብሪካ ተቋማት ያሳዩት፤ ከብርሃን

የፈጠነ ዕድገት ፤በዐለም ደረጃ የማፍያ ድርጅት ካልሆነ በስተቀር፤ ወያኔ በዚህ ረገድ ተደራጅቶ ይዘርፋል ብሎ ማመን ያስቸግራል ። ግን እየሆነ ነው ።። የታላላቅ ፕሮጀክቶችን ፤ ሥራና ግንባታ፤ ያለ ሌላ ተጫራች፤ በበቸኝነት የሚሻሙት የወያኔ ባልሟሎች ናቸው። ስግብግብነታቸው ደግሞ ፤ " አልጣግብ ባይ ሲተፋ ያድራል ። " የሚለውን ይትብሃል፤ የሚያሟሉ አድርጓቸዋል ። " **ዛሬ ፤በትግራይ ወርቃማ ዘመን** " ያልበላ፤ ምን ጊዜም ሊያልፍለት አይችልም ! የሚል የውስጥ መመሪያ መተላለፉን አምኖ፤ ሁሉም እንዳቅሙ ይዘርፋል ። " **ኢትዮጵያ ስተዘረፍ ፤ አብረህ ዘረፍ !** " የትግራይ ዘረኞች መፈክር ከሆነ ቆይቷል ።

ሙስና፤ አድላዊ፤ ቤተሰባዊና ዘውጋዊ ዝርፊያ ፤ የአደባባይ ምሥጠር ከሆነ ቆይቷል ብቻ ሳይሆን፤ የአገዛዙ ባኅርይና የሀገሪቱም ባኅል እስከ መሆን ደርሷል ። ዛሬ በሀገሪቱ የተስፋፋው ጉቦኝነት፤ ልክ በዐረብ ሀገር እንደ ተለመደው **መቁሹሽ** ማለት ነው። ጉቦኛነት ማፈሪያ ሳይሆን ፤ መስከበሪያና መታፈሪያ ሆኗል። የስድሳ ስድስቱ የካቲት ሕዝባዊ ዐብዮት ጥያቄና ዓላማ አፈር በልቷል። ዘውጋዊ አድሏዊነት የሚያሰፍር መሆኑ ቀርቶ፤ እንዲያውም፤ የሚያኮራ፤ የሚያሾም፤ የሚያሸልምና የሚያስመሰግን ሆኗል። የቆሳቁስና የነዋይ ማግበስበስ ስፋቱና መጠኑ፤ " ዛሬ ካልብላኽ ነገ ታካለኽ፤ አሁን ካልዘርፍኽ ፤ ኋላ ይቆጭሃል ፤እየተባባለ ሁሉም በየፈናው ፤ይቀማል፤ ይዘርፋል ፤ እርስ በዕርሱ ይጠቃቀማል ።ሌላው ኢትዮጵያዊ ፤ " ያፍዝዝ- ያደንዝዝ " ተደግሞበት፤ በገዛ ሀብቱ ፤ ንብረቱ ፤ ሀገሩ፤ ባይታዎር እና የበይ -ተመልካች እየሆኑ ጓጉቶ መቅረት ሆኗል ! ወያኔ ግን ሁለት መርጫዎቹን ሰጥተዋለች። ወይ እየተቃጠሉ መሞት፤ ያለዚያ ደግሞ ሀገር ጥሎ መሰደድ ! ይኽ የማይሆን ከሆነ ደግሞ ፤ የየራሱን፤ የየግሉን ምርጫ መውሰድ ከፈለገ ፤ የሚበድለውን እየገደሉ መሥዋዕት እየከፈሉ ታሪክ ሰርቶ ማለፍ ነው ! ያለዚያ ደግሞ፤ እየታሰሩ ወኅኒ/ ቃሊቲ መበስበስ !

ያም ሆነ ይኽ ፤ በምንም ዓይነት መንገድ ፤ እንዲህ የመሰለ ተስፋ አስቆራጭ ምርጫ ፤ ለሀገራችን ህዝብ አይገባውም ነበር ። " **ጊዜ ያመጣውን፤ ጊዜ እስኪመልሰው፤ መልካሙን ጊዜ መጠበቅ ነው** " የሚለው አነጋገር፤ ራስን ለሁኔታና ለጊዜ አስልፎ መስጠት ነው ። ይኽንን መቀበል አይገባም ። ሰው የጊዜ ባለቤት ሆኖ ጊዜን ሊጠቀምበት ይገባል እንጅ፤ ጊዜ ሰውን ሊገዛው አይገባም ። ዎያኔወቹ፤ አመችውን ጊዜ ተጠቀሙበት እንጅ፤ አመችውን ጊዜ እነርሱ አመጡት ብሎ መቀበል፤ በራሱ አሳማኝ አምክንዮ ( ሎጅክ ) አይደለም ። ብልሃትንና አቅምን አስተበብረን አመች ጊዜን ለመፍጠር የሚያግደን እንቅፋት መኖር የለበትም ። ይኽንን ለማድረግ ግን፤ **የጉንዳንን ጉልበት ፤ የሴትን ብልሃት ማግኘት ወሳኝ ነው።** " ክፉ ቀን ያልፋል እስኪያልፍ ግን ያለፋል" እየተባለ ፤ ክፉው ቀን ሳያልፍ፤ እኛም ሳያልፍልን፤ ዘመናችን ጨረስነው ። ክፉው ዘመን ግን ፤ በእኛ ጊዜ ስላልተወገደ፤ ለተተኪው ትውልድ እንዲተላለፍ እየተደረገ ነው ። የሚመጣው ትውልድ ሊወርስ የሚገባው፤ ሠላምና ፍቅርን ፤ አንድነትንና ኅብረትን ፤ መልካም አስተዳድርንና ብልፅናን ፤ ብሩኅ ተስፋንና ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን መሆን አለበት ። ለዚህ ዓላማ ተፈፃሚነት ተግተው የሚዋደቁ ልጆች ስለአሏት ኢትዮጵያ ፤ ብርኅታዊ ሀገር መሆኗ አይቀርም ።

በአሁኑ ጊዜ፤ በአንፃራዊነት፤ ወያኔ ሁለንተናዊ ኃይልና ጉልበት ያለው ሊመስል ይችል ይሆናል ። ግን አይደለም ! በመሠረታዊ መልኩ፤ ኃይሉ፤ ጉልበቱም፤ ብልሃቱም ፤ያለው በኢትዮጵያ ሕዝብ እጅ መሆኑ ማንም ሊጠራጠር አይችልም ። አይገባምም ።አሁን ማገናኘት የተሳነው፤ ኃይሉንና ብልሃቱን አውኅዶ ካለመገኘቱ ላይ ነው ።ይኽ ውኅደት ደግሞ መምጣጡ

አይቀሬ ነው ። የኢትዮጵያን ሕዝብ በየጊዜው የሚያስጮኸው ምን እንደሆነ መረዳት ከቻልን ፤ የወንዙን ውሃ ምን ያስጮኸዋል ? የሚለውን ጥያቄ መልስ መመልስ አንቸገርም ። የሚያስጮኸው፤ በወስጡ ያለው ድንጋይ ነውና !

ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኖራለች !